DISCOVER
ITS BEAUTY

ክፍል 6

# የመጨረሻው ወህይ



ዶ/ር ናጂ ኢብራሂም



# የመጨረሻው ወህይ

የተከበረው ቁርኣን በአላህ (አምላክ) ለነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የወረደው የመ ጨረሻው ወህይ (የመጨረሻው ኪዳን) ነው። ቁርአን የሰውን ልጅ ሕይወት ለመ ቆጣጠር እና ለማስተዳደር የወረደ መለኮታዊ ሕገ መንግሥት ነው።

ፍፁም በሆነው የፈጣሪ እውቀት ስለፍጥረቱ ይናገራል። እውነትን ይገልጣል እናም የሰው ልጅን ወደ እውነት መንገድ ይጋብዛል። ስለ ሰው እጣ ፈንታ ጠቃሚ መረጃ ይዟል። ሰዎችን ተረድተው ትምህርቶቹን በሥራ ላይ ለማዋል እንዲጥሩ በማስተማር እና ወደ ከፍተኛ መንፈሳዊ፣ ሥነ ምግባራዊ፣ አስተሳሰ ባዊ እና ማህበራዊ ደረጃቸውን ያሳድጋቸዋል።

ቁርአን ለመጨረሻው ነቢይ መሐመድ ለነቢይነቱ ማረጋገጫ የተሰጠ ዘላለማዊ ተአምር ነው፣ ልዩ እና ተወዳዳሪ የሌለው ነው። ምንም እንኳን ከአንድ ሺህ አራት መቶ ዓመታት በፊት የወረደ ቢሆንም፣ ዛሬም ቢሆን ሙሉ በሙሉ ሳይ ለወጥ እና ሳይቀየር (በመጀመሪያው አረብኛ መልክ) እናገኘዋለን።

አላህ በቁርዓኑ እንዲህ ይለናል፦

**“እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፡፡ እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን፡፡”** (15:9)

እንዲሁም አላህ በቁርኣኑ እንዲህ ይላል፦ **“«ሰዎችም ጋኔኖችም የዚህን ቁርኣን ብጤ በማምጣት ላይ ቢሰበሰቡ ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳት ቢሆንም እንኳ ብጤውን አያመጡም» በላቸው።”** (17፡88)




# ውብ የሆኑ የተከበረው ቁርዓን አንቀጾች

በዚህ ክፍል፣ ከማያልቀው የአላህ ቃል እና ጥበብ ውቅያኖሶች ውስጥ አንዳንድ የሚያምሩ ጥቅሶችን ላካፍላችሁ እወዳለሁ።

ስለእነዚህ ውብ እና ንፁህ የአላህ ብቸኛው እውነተኛ አምላክ ቃል የበለጠ ለማወቅ ቁርኣንን በራሳችሁ እንድታነቡ እጋብዛችኋለሁ። ትክክለኛ ትርጉም ያዘለውን ለማግኘት ይሞክሩ፤ ከአንዱ ታማኝ ኢስላማዊ ድረ-ገጽ በመስመር ላይ ማግኘት ይችላሉ። (እባክዎ በዚህ ጽሁፍ መጨረሻ ላይ የሚመከሩትን ኢስ ላማዊ ድረ-ገጾች ይመልከቱ)።

ሁሉም የቁርኣን አንቀፆች የአላህ ቃል ናቸው። በእስልምና ውስጥ አንዳንድ ወሳኝ እና ጉልህ የሆኑ አስተምህሮቶችን እና ፅንሰ-ሀሳቦችን በሚመለከት እስላ ማዊ እይታን የሚገልጹ አንዳንድ የተከበረ የቁርዓን አንቀጾችን በማንበብ እርካ ታን ማግኘት እንችላለን፣ ለምሳሌ፦

- የአላህ አንድነት፣ እውነተኛው አምላክ (ተውሂድ )
- ይቅር ባይነት እና ማዳን
- ፍትህ
- እኩልነት
- ሁለንተናዊ እና የመልእክት አንድነት
- አላህ እና መልክተኛው
- መረጋጋት እና ጀነት
- ወንዶች እና ሴቶች (በእስልምና)
- ታላላቅ ትምህርቶች
- አድርግ እና አታድርግ
- እርሱን ማስታወስ እና የአእምሮ ሰላም



# የአላህ (አምላክ) አንድነት (ተውሒድ) በተከበረው ቁርዓን

- **“አላህ ከርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም። ወደ ትንሣኤ ቀን በእርሱ ጥርጥር የሌለበት ሲኾን በእርግጥ ይሰበስባችኋል። በንግግርም ከአላህ ይበለጠ እውነተኛ ማነው?”** (4:87)

- **“ይህ ጌታችሁ አላህ ነው፡፡ ከእርሱ በቀር (በእውነት የሚመለክ) አምላክ የለም፡፡ ነገርን ሁሉ ፈጣሪ ነው፡፡ ስለዚህ ተገዙት፡፡ እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ተጠባባቂ ነው፡፡”** (6፡102)

- **“እናንተ ሰዎች ሆይ! በእናንተ ላይ (ያለውን) የአላህን ጸጋ አስታውሱ፡፡ ከአላህ ሌላ ፈጣሪ አለን? ከሰማይና ከምድርም ሲሳይን የሚሰጣችሁ አለን? ከእርሱ በስተቀር አምላክ (ሰጪም) የለም፡፡ ታዲያ ወዴት ትዞራላችሁ፡፡”** (35:3)

- **“እርሱም አላህ ነው፡፡ ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም፡፡ ምስጋና በመጀመሪያይቱም በመጨረሻይቱም ዓለም ለእርሱ ብቻ ነው፡፡ ፍርዱም የእርሱ ብቻ ነው፡፡ ወደእርሱም ትመለሳላችሁ፡፡”** (28:70)

- **“አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው፤ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም። (እርሱ) እጅግ በጣም ርኅሩህ አዛኝ ነው፡፡”** (2፡163)

- **“በል "እርሱ አላህ አንድ ነው። አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው። አልወለደም፤ አልተወለደምም። ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም።"”** (112፡1-4)

- **“ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለውን አንድን አምላክ ሊገዙ እንጂ ያልታዘዙ ሲኾኑ ሊቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸውን፣ የመርየምን ልጅ አልመሲሕንም ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ፡፡ ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው፡፡”** (9:31)

በእርግጥም የአላህ ብቸኝነት (በአረብኛ፣ **ተውሒድ**) ላይ ንፁህ እና ግልጽ የሆነ ፅንሰ-ሀሳብ የቁርኣን አስፈላጊ ጭብጥ ነው።



**“በላቸው «እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ፡፡ አላህ ኃጢኣቶችን በመላ ይምራልና፡፡ እነሆ እርሱ መሓሪው አዛኙ ነውና፡፡»”** (39:53)

አንዲት ነፍስ ተጸጽታ ወደ አላህ ስትመለስ አላህ ወደ ባሪያው ተቀባይና ምህረትን ይመለሳል። አዎን፣ አላህ ወደርሱ በቅንነት ስንመለስ ወንጀሎችን ሁሉ ይምራል። እንዴት ያለ ታላቅ ነገር ነው!

**“አላህ (ከኃጢኣት) ተመላሾችን ይወዳል፤ ተጥራሪዎችንም ይወዳል በላቸው።”** (2፡222)

በእስልምና፤ አላህ የሰላም፣ የምህረት እና የይቅርታ ምንጭ ሆኖ ነው የሚታየው እንጂ የጥላቻ፣ የደም መፋሰስ እና የሽብርተኝነት ምንጭ አይደለም።

ስለዚህ መዳንን እና ዘላለማዊ ህይወትን ለማግኘት በቀላሉ ወደ አላህ ተመለሱ፣ በእርሱ ብቻ አምናችሁ መልካም ስራዎችን ስሩ። ንጹሕ፣ ጨዋ ሰው ሌሎች የሠሩትን ኃጢአት ለመክፈል እና ለማጥፋት መሰቀል ወይም መገደል አያስፈልገውም። እስልምና ተከታዮቹ (ሙስሊሞች) ሌሎችን ይቅር እንዲሉ ያዘል።

ይህ በእስልምና ውስጥ ያለውን ቆንጆ የመዳን እና የይቅርታ ጽንሰ-ሀሳብ ባጭሩ አብራርቷል ይህም በእርግጥ የምህረት እና የይቅርታ ሀይማኖት ነው።



**"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ለአላህ ቀጥተኞች በትክክል መስካሪዎች ኹኑ። ሕዝቦችንም መጥላት ባለማስተካከል ላይ አይገፋፋችሁ። አስተካክሉ። እርሱ (ማስተካከል) ለአላህ ፍራቻ በጣም የቀረበ ነው። አላህንም ፍሩ። አላህ በምትሠሩት ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው።"** (5:8)

እስልምና ወዳጅም ጠላትም በማንኛውም ጊዜ በሰላምም ይሁን በጦርነት ፍትሀዊ እንድንሆን ያስተምረናል። ከግለሰባዊ ፍላጎት ወይም ከማህበራዊ እና ባህላዊ ሁኔታዎች ጋር በተያያዙ ለውጦች ምክንያት የሞራል እሴቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ይቀየራሉ ከሚል አስተሳሰብ ነፃ በሆነ ሁኔታ ራሳችንን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ፍትህ እና ስነምግባር እንድንመራ ያስተምረናል።

**"አላህ አደራዎችን ወደ ባለቤቶቻቸው እንድታደርሱ ያዛችኋል። በሰዎችም መካከል በፈረዳችሁ ጊዜ በትክክል እንድትፈርዱ (ያዛችኋል)።"** (4:58)

እስልምና የውበቱ እና ዘላለማዊ የእዝነት እና የፍትህ እሴቶቹ ተግባራዊ መገለጫ በመሆኑ የሙስሊም ሊቃውንት **'አምስቱ አስፈላጊ ነገሮች'** ብለው የሚጠሩትን እንድንጠብቅ አዞናል።

- **ሃይማኖት**
- **ነፍስ**
- **አእምሮ**
- **ክብር**
- **ገንዘብ እና ንብረት**



በሚያምር ሁኔታ፣ የተከበረው ቁርኣን አንድ ሰው ንፁህ ነፍስን ከገደለ፣

**"... ነፍስን የገደለ ሰው ሰዎቹን ሁሉ እንደገደለ ነው፤ ሕያው ያደረጋትም ሰው ሰዎቹን ሁሉ ሕያው እንዳደረገ ነው"** (5:32)

የእምነት ነፃነትና ጥበቃን በተመለከተ የተከበረው ቁርኣን እንዲህ ይላል፡- **"በሃ ይማኖት ማስገደድ የለም..."** (2፡256)።

ስለዚህም እስልምና የሰውን ልጅ ያከብራል እንጂ ማንንም ሰው እምነቱን እን ዲቀበል ማስገደድን አይቀበልም። ሙስሊም ካልሆኑ ሰዎች ጋር ባለው መስ ተጋብር የእስልምና እውነት፣ ውበት፣ ፍትህ፣ ደግነት እና መቻቻል ይህ ነው። በተጨማሪም እስልምና ሌሎችን በምንፈርድበት ጊዜ ሐቀኛ፣ ተጨባጭ እና ሚዛናዊ እንድንሆን አዘናል።

አላህ በተከበረው ቁርኣን ላይ የነገረንን እናስታውስ፡-

**"...ሕዝቦችንም መጥላት ባለማስተካከል ላይ አይገፋፉችሁ። አስተካ ክሉ። እርሱ (ማስተካከል) ለአላህ ፍራቻ በጣም የቀረበ ነው።"** (5:8)

የሆነ ሆኖ እስልምናን እና ሙስሊሞችን በሙሉ በአሸባሪነት የሚወቅሱ እና እስ ልምና የተስፋፋው በሰይፍ ነው የሚሉ ኢ-ፍትሃዊ የፖለቲካ እና የሃይማኖት መሪዎች፣ ጸሃፊዎች፣ የታሪክ ተመራማሪዎች እና የሚዲያ ሰዎች አሉ፤ እውነ ተኛ አምላክ የሆነውን አላህን ከመጨረሻው ነብዩ ሙሐመድ ጋር በከፋ እና አስ ቀያሚ ምስሎች፣ ፊልሞች እና ካርቶኖች ላይ ያለ ፍትሃዊ እና አክብሮት የጎደ ለው ድርጊት የሚያሳዩ አሉ።



# እነዚህን ጥያቄዎችን ግምት ውስጥ አስገቡ

- ይህ ማለት ነፃነትና በተለይም የመናገር ነፃነት ማለት ነው? ወደ እስልምና እና ሙስሊሞች ሲመጣ ድርብ መስፈርት የለም?
- ለምንድነው 'የክርስትና ሽብርተኝነት/ሽብርተኞች'፣ 'የአይሁድ ሽብርተኝነት/አሸባሪዎች'፣ 'የሂንዱ አሸባሪነት/አሸባሪዎች'፣ ወይም 'ቡድሂስት ሽብርተኝነት/አሸባሪዎች'፣ አልፎ አልፎ እንኳን በመገናኛ ብዙኃን የማይሰማው?
- ለምንድነው ሽብርተኝነት በእስልምና እና በሙስሊሞች ላይ ብቻ የተፈረጀው? በሌሎች የሚፈጸመው ሽብር እና ጥቃትስ?
- ሁሉም ሰው ሌላውን እና እምነታቸውን ለመስደብ፣ ለመርገም እና ለመናቅ ወይም ሁሉንም በአሸባሪነት ለመወንጀል ነፃ ነው?
- ስልጣኔን፣ ዲሞክራሲን እና ነፃነትን ለወጣቱ ትውልድ በትምህርት ቤቶች፣ በኮሌጆች እና በአጠቃላይ ማህበረሰቡ የሚያስተምሩት እንደዚህ ነው?
- በአሁን ሰዓት በአለም ላይ ብዙ ጥበበኞች፣ ተጨባጭ፣ ቅን እና ነጻ አስተሳሰብ ያላቸው ወንዶች እና ሴቶች እስልምናን እንዲቀበሉ ያደረገው የእስልምና ሰይፍ ነውን? (እነዚህ ወንድሞች እና እህቶች ለምን ወደ እስልምና እንደተመለሱ የሚያብራሩ ብዙ መጽሃፎች፣ መጣጥፎች፣ ታሪኮች፣ ድረ-ገጾች እና የቪዲዮ እና የማህበራዊ ሚዲያ ፅሁፎች አሉ። ለምሳሌ እስልምና የኛ ምርጫ፡- የዘመናዊ አሜሪካውያን ሙስሊም ሴቶች ምስል፣ የሚለውን በዴብራ ኤል. ዲርክስ እና ስቴፋኒ ፓርሎብ የተሻሻለውን መፅሐፍ እንድታነቡ እመክራለሁ።)

**ማሳሰቢያ፡- ምንም እንኳን አሉታዊ መግለጫዎች ቢኖሩም፣ የምዕራባውያን መገናኛ ብዙኃን ግን እስልምና በዓለም ላይ ካሉት ሀይማኖቶች በፍጥነት እያደገ ያለ ሃይማኖት እንደሆነ ዘግቧል። ታዲያ ለምን እስልምናን?**



# እኩልነት በተከበረው ቁርዓን

**"እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፡፡ እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፡፡ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፡፡ አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው፡፡"** (49:13)

ይህንን የእኩልነት ጽንሰ ሃሳብ በእስልምና እምነት ውስጥ ያረጋገጡት ነቢዩ ሙሐመድ በመጨረሻው ስብከታቸው ላይ፡-

**"እናንተ ሰዎች ሆይ አምላካችሁ አንድ ነው፤ አባታችሁም አንድ ነው፤ ሁላችሁም ከአደም ናችሁ፣ አደምም ከአፈር ነው፣ አረብ አረብ ካል ሆነው አይበልጥም። አረብ ያልሆነውም ከአረብ አይበልጥም። ነጭ ከጥቁር አይበልጥም፣ ጥቁርም ከነጭ አይበልጥም። ሁላችሁም እኩል ናችሁ። በመልካም ሥራ ካልሆነ በቀር ማንም በሌሎች ላይ የበላይነት የለውም።"**

- እስልምና ሌሎችን በዘራቸው፣ በቆዳ ቀለም እና በዜግነታቸው እንዳንጠላ ወይም እንዳንንቅ ያስተምረናል፡፡
- እስልምና አለም ለሚመሰክረው የዘር ግጭት መቅሰፍት ተግባራዊ መፍትሄ ነው፡፡

በእስልምና ጥቁሮች እና ነጮች በአንድ የሰው ዘር ውስጥ ወንድማማቾች እና እህትማማቾች ናቸው፡፡ እኛ ሁላችንም ከአፈር ከተፈጠረው ከአንዱ አባት ከአደም የተወለድን ነን፡፡ ስለዚህ ሁላችንም ከምድር ነን፣ ሁላችንም ወደ ምድር ተመልሰን ወደ አፈር እንመለሳለን፡፡

ይህ ጠቃሚ ትምህርት የተወሰደው ከላይ ከተጠቀሱት የቁርኣን እና የነብያት የመጨረሻ ስብከት ጥቅሶች ነው። ታዲያ አንዳንድ ሰዎች ለምን የውሸት ኩራት ይሰማቸዋል ወይም በሌሎች ላይ በትዕቢት ይሠራሉ?



# ሁለንተናዊነት እና የመልእክት አንድነት

ሙስሊሞች ሁሉንም የአላህ ነቢያትን ማለትም አደም፣ ኑህ፣ ኢብራሂም፣ ኢስማዒል፣ ኢስሐቅ፣ ያዕቁብ፣ ሙሳ፣ ዒሳ እና ሙሐመድ (የአላህ በረከት እና ሰላም በእነርሱ ላይ ይሁን) ይወዳሉ እናም ያምናሉ።

ቁርኣን **እንዲህ ይላል፡-**

**“«በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርኣን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስ ማዒልና ወደ ኢስሐቅም ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተ ሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንኾን አመንን፤ እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን» በሉ፡፡”** (2፡136)

ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

**“እኔ ከሰዎች ሁሉ የመርየም ልጅ ዒሳ ጋር በጣም ቅርብ ነኝ በእኔና በእርሱ መካከል ሌላ ነብይ አልነበረምና። ነቢያት ወንድማማቾች ናቸው፤ እናቶቻቸው የተለያዩ ናቸው ሃይማኖታቸው ግን አንድ ነው።”**

**ታዲያ ይህ ሁለንተናዊ፣ አንድ እውነተኛ የአላህ ነቢያት ሃይማ ኖት ምንድን ነው?**



# ልናስብባቸው የሚገቡ ሌሎች ውብ አንቀፆች

የተከበረው ቁርአን ውበት፣ ጥፍጥና እና ንፅህናው ገደብ የለሽ ነውና ያለምንም አይነት ማብራሪያ በቀላሉ አንዳንድ የቁርኣን አንቀጾችን ልጥቀስ። ብታሰላስሉ እና ብታስቡባቸው ደስ ይለኛል። ከመጨረሻው ኪዳን ከቁርኣን ብዙ እውቀት ለማግኘት ሞክሩ።

- **አላህ እና መልክተኛው**


**"እርሱ ያ (አላህ) መልክተኛውን (ሙሐመድን) በመሪ መጽሐፍና በእውነተኛ ሃይማኖት በሃይማኖት ሁሉ ላይ ሊያልቀው የላከ ነው።"** (48፡28)

**"ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም፡፡ ግን የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው፡፡ "አላህም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው"** (33:40)

- **መረጋጋት እና ጀነት**

**"እርሱ ያ በምእምናን ልቦች ውስጥ ከእምነታቸው ጋር እምነትን ይጨምሩ ዘንድ እርጋታን ያወረደ ነው፡፡ ለአላህም የሰማያትና የምድር ሰራዊቶች አልሉት፡፡ አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው፡፡ ምእምናንንና ምእምናትን ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲኾኑ ሊያገባቸው ከነርሱም ኃጢአቶቻቸውን ሊያብስላቸው (በትግል አዘዛቸው)፡፡ ይህም ከአላህ ዘንድ የኾነ ታላቅ ማግኘት ነው፡፡"** (48፡4-5)

**"(ለአመነች ነፍስም) «አንቺ የረካሺው ነፍስ ሆይ!) ወዳጅ ተወዳጅ ኾነሽ ወደ ጌታሽ ተመለሺ፡፡ በባሮቼም ውስጥ ግቢ። ገነቴንም ግቢ፤» (ትባላለች)፡፡"** (89፡27-30)



- **ወንዶች እና ሴቶች በእስልምና**

**"ሙስሊሞች ወንዶችና ሙስሊሞች ሴቶች፣ ምእምናንና ምእምናትም፣ ታዛዦች ወንዶችና ታዛዦች ሴቶችም፣ እውነተኞች ወንዶችና እውነተኞች ሴቶችም፣ ታጋሾች ወንዶችና ታጋሾች ሴቶችም፣ አላህን ፈሪዎች ወንዶችና አላህን ፈሪዎች ሴቶችም፣ መጽዋቾች ወንዶችና መጽዋቾች ሴቶችም፣ ጿሚዎች ወንዶችና ጿሚዎች ሴቶችም፣ (ካልተፈቀደ ሥራ) ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች ወንዶችና ጠባቂ ሴቶችም፣ አላህን በብዙ አውሺዎች ወንዶችና አውሺዎች ሴቶችም፣ አላህ ለእነርሱ ምሕረትንና ታላቅን ምንዳ አዘጋጅቶላቸዋል።"** (33፡35)

**"ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ኾኖ ከበጎ ሥራዎች አንዳችን የሚሠራም ሰው እነዚያ ገነትን ይገባሉ።"** (4፡124)

- **ምርጥ ትምህርቶች**

**"ከጌታችሁ ወደ ኾነችም ምሕረትና ስፋትዋ እንደ ሰማያትና ምድር ወደ ኾነች ገነት አላህን ለሚፈሩ የተዘጋጀች ስትኾን ተቻኮሉ። ለእነዚያ በድሎትም ኾነ በችግር ለሚለግሱት፣ ቁጪትንም ገቺዎች ከሰዎችም ይቅርታ አድራጊዎች ለኾኑት (ተደግሳለች)። አላህም በጎ ሠሪዎችን ይወዳል። ለእነዚያም መጥፎ ሥራን በሠሩ ወይም ነፍሶቻቸውን በበደሉ ጊዜ አላህን የሚያስታውሱና ለኀጢአቶቻቸው ምሕረትን የሚለምኑ ለኾኑት ከአላህ ሌላ ኀጢአቶችን የሚምር ማነው? (አንድም የለም)። (በስሕተት) በሠሩትም ላይ እነርሱ የሚያውቁ ሲኾኑ የማይዘወትሩ ለኾኑት (ተደግሳለች)። እነዚያ ምንዳቸው ከጌታቸው ምሕረትና በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲኾኑ በሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶችም ናቸው። የሠሪዎችም ምንዳ (ገነት) ምንኛ አማረች!።"** (3፡133-136)



- **አድርግ እና አታድርግ**

**"...አላህን እንጂ ሌላን አታምልኩ፤ በወላጆችም በጎን ሥራ (አድርጉ)፤ በዝምድና ባለቤቶችም፣ በየቲሞችም (አባት የሌላቸው ልጆች) በምስኪኖችም (በጎ ዋሉ)፤ ለሰዎችም መልካምን ተናገሩ..."** (2፡83)

- **አላህን ማስታወስ እና የአእምሮ ሰላም**

**"(እነሱም) እነዚያ ያመኑ ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው። ንቁ! አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ፡፡"** (13:28)

በእርግጥም የተከበረው ቁርኣን እውነታዎች፣ ጥቅሞች እና ድንቆች መጨረሻ የላቸውም። ባነበብነው ቁጥር ብዙ ግኝቶችን እናገኛለን እና በእያንዳንዱ ጊዜ ቁርኣንን ለመጀመሪያ ጊዜ እያነበብን እንደሆነ ይሰማናል።
የቁርአንን ትክክለኛነት፣ የቋንቋ ልቀት፣ ሳይንሳዊ እውቀቱን እና የህክምና መድሀኒቶችን ጨምሮ ሌሎች በርካታ አስደናቂ የቁርኣን ገጽታዎች የሚገልፁ ይህን ክፍል ለማሳጠር ሲባል ብዙ ያላነሳናቸዉ ነጥቦች አሉ።



# የማወቅ ጉጉት አልዎት?

የማወቅ ጉጉት ካሎት እና ስለ እስልምና ተጨማሪ መረጃ እና ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ እባክዎን ድረ-ገጻችንን ይጎብኙ፡-

**www.discoveritsbeauty.com**

## የውበቱን ያግኙ ተከታታይ ቡክሌቶች፡-

1. ከብዙው በትንሹ
2. የአደም እና የሐዋ ሃይማኖት
3. የእስልምና መሠረቶች
4. የሰብአዊነት ወሳኝ ጥያቄዎችን መመለስ
5. የእርሱ መልካም ስሞች
6. የመጨረሻው ወህይ
7. የመጨረሻው መልእክተኛ

## ጠቃሚ ኢስላማዊ ድረ-ገጾች፡-

http://www.allahsquran.com
http://www.quranexplorer.com
http://www.islamhouse.com
http://www.edialogue.org
http://www.islamreligion.com
http://www.newmuslimguide.com
http://www.guidetoislam.com/en/

# የእምነት ምስክርነት (የእስልምና መግቢያ በር)

“ከአላህ በስተቀር በእውነት እና በብቸኝነት የሚመለክ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ ሙሐመድም የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ።”

በአረብኛ እንዲህ ይነበባል፡-

أشهد أن لا إله إلا الله وأشهد أن محمداً رسول الله

ሲነበብ ይህን ይመስላል፡-

**አሽ-ሀዱ አላ ኢላሀ ኢለ ሏህ**

**ወ አሽ-ሀዱ አነ ሙሐመደን ረሱሉሏህ**

ይህ አንድ ሰው እስልምናን ለመቀበል በአፉ መናገር ያለበት የእምነት ምስክርነት ነው። የእስልምናን እውነተኝነት፣ ውበት እና ቀላልነት አንድ ላይ ይዟል።



DISCOVER

ITS BEAUTY

www.discoveritsbeauty.com

ይቃኙት


GLOBAL ACADEMY FOR TRANSLATION AND EDUCATION (GATE)
LONDON | THE UNITED KINGDOM

በAL-ANDALUS GROUP LTD የተተረጎመ
www.alandalusgroup.org

كتاب الوحي الأخير باللغة الأمهرية